# ኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት አገልግሎት፡፡
# Ethiopia: The Kingdom of God Services

---

ኢትዮጵያውያንና ኢትዮጵያውያት፥
በሚገኙበት በማናቸውም ቦታና የኑሮ ዓይነት፥
በግለሰብ፥ በቤተሰብና በኅብረተሰብ አንድነት፡
በሓመረ ኖኅ ኪዳነ ምሕረት ቤተ ክርስቲያንነት፥
በመንፈስ ቅዱስ ጸጋና በረከት በተሰበሰቡበት፥
በመስከረም አንድ ቀን፡ በርእሰ ዓውደ ዓመት፥
በድንግል ማርያም እና በኢየሱስ ክርስቶስ ልደታት፥
በእነርሱ የተገኘውን ዓመተ ምሕረት፥
በአዳምና ሔዋን፥ የዓለሙን ፍጥረት፥
በቅዱሱ ኪዳን፡ የኢትዮጵያን ነጻነት፥
ተቀብለው የጸኑባትን፡ የእግዚአብሔርን መንግሥት፥
በታላቅ በዓልነት የሚያከብሩበት ሥርዓት ጸሎት፡፡

---

በቅዱስ መስቀል ማኅተም ምልክትነት
በ፬ቱ ማዕዘን የሚፈጸም የቅዳሴ ሥርዓት፡፡

<u>፩ኛ፡ በምዕራቡ ማዕዘን፤</u>

ስለርእሰ ዓውደ ዓመተ ምሕረት፥

ምንባብ፡-

ሮሜ ምዕ. ፲፫፥ ቁ. ፰-፲፬፤
ራእ. ምዕ. ፳፩፥ ቁ. ፩-፰፤
ሐዋ. ምዕ. ፫፥ ቁ. ፲፱-፳፮፡፡

ምስባክ፡- መዝ. ፷፬፥ ቁ. ፲፩-፲፪፤

| | |
|---|---|
| ወትባርክ፡ አክሊለ ዓመተ ምሕረትከ፤ | የምሕረትህን ርእሰ ዓውደ ዓመት፡ ትባርካለህ፤ |
| ወይጸግቡ፡ ጠላተ ገዳም፤ | ምድረ በዳው፡ በልምላሜ ይሸፈናል፤ |
| ወይረውዩ፡ አድባረ በድው፡፡ | የበረሃ ተራሮች፡ በዝናብ ይረካሉ፡፡ |

ወንጌል፡- ሉቃ. ምዕ. ፬፥ ቁ. ፲፬-፳፱፡፡

## <u>፪ኛ፡ በሰሜኑ ማዕዘን፤</u>

### ስለቅዱሱ ኪዳን፡ የኢትዮጵያን ነጻነት፤

ምንባብ፡- ዕብ. ምዕ. ፯፥ ቁ. ፩-፲፤
ራእ. ምዕ. ፭፥ ቁ. ፩-፲፤
ሐዋ. ምዕ. ፰፥ ቁ. ፳፯-፴፱፤

ምስባክ፡- መዝ. ፷፯፥ ቁ. ፴፩-፴፪፤

| | |
|---|---|
| ኢትዮጵያ ታበጽሕ እደዊሃ ኀበ እግዚአብሔር፤ | ኢትዮጵያ፡ እጆቿን ወደእግዚአብሔር ትዘረጋለች፤ |
| ነገሥተ ምድር፡ ሰብሕዎ ለእግዚአብሔር፤ | የምድር ገዢዎች፡ እግዚአብሔርን አመስግኑ፤ |
| ወዘምሩ ለአምላክነ፡፡ | ለአምላካችንም ዘምሩ፡፡ |

ወንጌል፡- ማቴ. ምዕ. ፲፪፥ ቁ. ፴-፵፪፡፡

## <u>፫ኛ፡ በደቡቡ ማዕዘን፤</u>

### ስለቅድስት ድንግል ማርያም

ምንባብ፡- ዕብ. ምዕ. ፱፥ ቁ. ፩-፭፤
ራእ. ምዕ. ፲፩፥ ቁ. ፲፭-፲፱፤
ሐዋ. ምዕ. ፩፥ ቁ. ፯-፲፬፡፡

ምስባክ፡- መዝ. ፻፴፩፥ ቁ. ፲፫-፲፬፤

| | |
|---|---|
| እስመ ኃረያ እግዚአብሔር ለጽዮን፤ | እግዚአብሔር ጽዮንን መርጧታልና፤ |
| ወኣብደራ፡ ከመ ትኩኖ ማኅደሮ፤ | ማደሪያውም፡ ትኾነው ዘንድ ወዷታልና፤ |
| ዛቲ ይእቲ፡ ምዕራፍየ ለዓለም፡፡ | “ይህች፡ ለዘለዓለም ማረፊያዬ ናት!” አለ፡፡ |

ወንጌል፡- ሉቃ. ምዕ. ፩፥ ቁ. ፳፯-፶፯፡፡

## <u>፬ኛ፡ በምሥራቁ ማዕዘን፤</u>

### ስለኢየሱስ ክርስቶስ ልደት፤

#### የፍሬ ቅዳሴ፡

ምንባብ፡- ገላ. ምዕ. ፬፥ ቁ. ፩-፯፤
፩ኛ ዮሐ. ምዕ. ፬፥ ቁ. ፩-፲፭፤
ሐዋ. ምዕ. ፲፫፥ ቁ. ፲፯-፴፫፡፡

ምስባክ፡- መዝ. ፪፥ ቁ. ፯-፰፤

| | |
|---|---|
| እግዚአብሔር ይቤለኒ ወልድየ አንተ፤ | እግዚአብሔር አለኝ፡ “አንተ ልጄ ነህ!” |
| ወአነ ዮም ወለድኩከ፤ | እኔ፡ ዛሬ ወለድሁህ፤ |
| ሰኣል እምኔየ፡ እሁበከ አሕዛበ ለርስትከ፡፡ | ለምነኝ! አሕዛብን፡ ለርስትህ እሰጥሃለሁ፡፡ |

ወንጌል፡- ሉቃ. ምዕ. ፪፥ ቁ. ፩-፳፡፡

## <u>የልደት ዝማሬ</u>

አማን፡ በአማን፡ አማን፡ በአማን፤ አማን፡ በአማን፡ አማን፡ በአማን፤

መንክር ስብሓተ ልደቱ! መንክር ስብሓተ ልደቱ።

### <u>ትርጉም</u>

እውነት በእውነት! እውነት በእውነት ! እውነት በእውነት! እውነት በእውነት !

የክርስቶስ የልደቱ ገናናነት ዕፁብ ድንቅ ነው! የክርስቶስ የልደቱ ገናናነት ዕፁብ ድንቅ ነው!

## <u>የምሥራች ሰላምታ</u>

በዚህ በዓልና ከዚህ ቀን ጀምሮ፡ እስከ በዓለ ግዝረቱ፥ ከዚያም፡ እስከ በዓለ በአተ መቅደሱ ድረስ፡ ካህናትና ምእመናን፥ እርስ በርሳቸውም የሚለዋወጡት የምሥራች ቃል፦

ከመስከረም ፩ እስከ ፳ ቀን፦

*"ዮም ፍሥሓ ኮነ!"* *"በእንተ ልደቱ ለክርስቶስ!"*
"ዛሬ ደስታ ኾነ!" "የክርስቶስ የልደቱ በዓል ነውና!"

ከመስከረም ፳ እስከጥቅምት ፲ ቀን፦

*"ዮም ፍሥሓ ኮነ!"* *"በእንተ ግዝረቱ ለክርስቶስ!"*
"ዛሬ ደስታ ኾነ!" "የክርስቶስ የግዝረቱ በዓል ነውና!"

በጥቅምት ፲ ቀን፦

*"ዮም ፍሥሓ ኮነ!"* *"በእንተ በአተ መቅደሱ ለክርስቶስ!"*
"ዛሬ ደስታ ኾነ!" "ክርስቶስ፡ ወደቤተ መቅደስ የገባበት ቀን ነውና!"

ይህ የደስታ መንፈስና ሥርዓት፡ እስከጥቅምት ፲ ቀን ይቀጥላል።

---